# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## ፕሬዝደንት ባራክ ኦባማ፣ እነሱና እኛ፤

የክቡር ባራክ ኦባማ የመጀመሪያው ጥቁር የዩናትድ ስቴትስ ፕሬዝደንት ሆኖ መመረጥ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡ ታሪካዊነቱ በቆዳቸው ቀለም ብቻ አይወሰንም፡፡ አይደለም፡፡ ከዚኽ ባላነሰ ሁኔታ ሊጠቀስ የሚገባው አንድ ቁም ነገር አለ፡፡ ኦባማ የአሜሪካ ፕሬዝደንት ሆነው ለመመረጥ የበቁት መጀመሪያውኑ ቀደም ሲል በምርጫው ሂደት ለመሳተፍ ማንም ሳያግዳቸው ራሣቸውን ሲያገልሉ የነበሩ ጥቁሮችና ወጣቶች በዚች አገር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ፖለቲካው ሂደት ውስጥ በገፍ በመግባት ሚዛን የደፉ ተሳትፎ በማድረጋቸው እንደሆነ ምርጫውን አስመልክቶ የወጡ አሃዞች ሁሉ የሚያሳዩት ጉዳይ ነው፡፡ የባራክ ኦባማ ለምርጫ መቅረብና ማቸነፍ በዚኽ ከፍተኛ መነቃቃትና ተስፋ የፈጠረው በአገራቸው በአሜሪካ ብቻ አይደለም፡፡ ይኽ ምርጫ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ቢሆን ከዚኽ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መልክ ከዳር-እስከ-ዳር የሕዝቦችን ቀልብ የሳበና የተስፋ ስሜት ያጫረ መሆኑ ታይቷል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም በከተሞች፣ ይኽንን ምርጫ ልክ እንደራሱ አገር ምርጫ አድርጎ ሲከታተል እንደነበርና የዩናይትድ ስቴትስ ዜግነት ያላቸው ኢትዮጵያዊ-አሜሪካውያን ብቻ ሣይሆኑ ሌሎችም ዜጎቻችን የባራክ ኦባማን ተወዳዳሪነት ደግፈው ባደረጉት ከፍተኛ ተሳትፎ በአንዳንድ ቦታዎች ለሳቸው መመረጥ የማይናቅ አስተዋጽዖ እንዳደረጉ አይተናል፡፡ ከዚኽ የድጋፍ እንቅስቃሴ ጀርባ ያለው ምኞትና ስሌት አገራችንን ከተተከለባት አሸባሪ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት በሚደረገው ትግል የባራክ ኦባማ የአሜሪካ አስተዳደር ከእንቅፋትነት አልፎ በደጋፊነት ይሰለፋል ከሚል ተስፋ እንደሆነ ግልጽ ይመስለናል፡፡ እርግጥ ኦባማ ወደ ፕሬዝደንትነት ካደረጉት ጉዞ፣ በምርጫው ዘመቻ ወቅት ብቻ ሳይሆን ከቀደመ የፖለቲካ ሕይዎት ታሪካቸው፣ ከአፍሪቃ አህጉርና ከጥቁር ሕዝቦች ጋር ካላቸው የትውልድ ትስስር፣ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመኖር ስለውጭው ዓለም ካላቸው ቀጥተኛ የግል የሕይዎት ልምድና ከቀሰሙት ተሞክሮ፣ ከልዩ ልዩ ባሕሎች፣ እምነቶችና አስተሳሰቦች ጋር ካላቸው ትውውቅ ሁሉ አንፃር ሲታዩ የዓለም ሕዝቦች ችግርና ጉጉት ይበልጥ የሚገባቸው እንደሆኑና እነዚህን ችግሮች ለመፍታት፣ እነዚህን የሕዝቦች ምኞቶችና ፍላጎቶች እውን ለማድረግ በሚደረገው ትግል በፀጥታና በመረጋጋት ስም አፋኞችና ጨቋኞች የሚያደርሱትን ግፍ እያዩ እንዳላዩ መሆንን የመረጡትና "አንድ ወጥ" አስተሳሰብ ከነበራቸው ጆርጅ ቡሽ የተሻለ የሕዝብን ሰቆቃና ተሃስቦ ለማስተባቃት ይበልጥ የተመቻቹ እንደሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም፡፡

ከዚኽ አንፃር ሲታይ ፕሬዝደንት ኦባማ በምረቃቸው ወቅት በአደረጉት ንግግር "በሙስና፣ በማጭበርበርና ተቃውሞን በማፈን ሥልጣንን የሙጥኝ ያላችሁ ክፍሎች፣ ከታሪክ አንፃር በተሳሳተ ጎራ መሆናችሁን እወቁ!" ማለታቸው በመላው ዓለም በአፋኝና ሙሰኛ አገዛዞች ሥር ለሚማቅቁ ሕዝቦች ይኽ ነው የማይባል ተስፋ የሰጠ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

ይኽም ሆኖ ከአንዳንድ ወገኖቻችን እንደሚሰነዘረው በባራክል ኦባማ መመረጥ የኢሕአዴግ መሪዎች "ብርክ ይዟቸዋል" የሚባልበት ድረጃ ላይ ናቸው ማለት አይቻልም፡፡ ለዚኽ ደግሞ ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አሉ፡፡ አንደኛ ቀደም ሲል ከነበሩ የአሜሪካ አስተዳደሮች አካሄድ የቀሰሙት ትምህርት አለ፡፡ ሁለተኛ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች የተፈጠረውን "አዲስ ሁኔታ" ለመጠቀም ብቃት አይኖራቸውም የሚለው የንቀት ስሌታቸው አለ፡፡

**ዋና መሥሪያ ቤት** (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
ስልክ ቁ./Tel. 202 361 7162

**አውሮጳ** (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132

የአሜሪካ አስተዳደሮችን የቆየ አካሄድ ስንመለከት የፕሬዝደንት ኦባማ አነጋገር ምንም አዲስ ነገር የለውም፡፡ የአሜሪካ ፕሬዝደንቶች በኋላ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ቀርቶ አመርቂ ጅማሮ ማድረግ አይታይባቸውም እንጂ የምረቃ ንግግራቸው ላይ በዓለም ነፃነትና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ አዲሱ የአሜሪካ አስተዳደር ለነዚህ ቅዱስ ዓላማዎች ከሚታገሉ ሕዝቦች ጎን ተሰልፎ አፋኝ፣ ሙሰኛና ያለ ሕዝብ ይሁንታ አገር የሚገዙና ሕዝባቸውን የሚጨቁኑ ኃይሎችን በቁርጠኝነት እንደሚዋጋ ማብሰር ያለ፣ የተለመደና የተደጋገመ ነገር ነው፡፡ ጆርጅ ቡሽም ቢሆኑ ከዚኽ አንፃር እንደ ባራክ ኦባማ ብቻ ሳይሆን ከሳቸውም በባሰ አፋኝ መሪዎችን "ከማስጠንቀቅ" እና ታጋይ ሕዝቦችን ደግሞ "በርቱ ከጎናችሁ ነን" ብለው ከማበረታታት ወደ-ኋላ አላሉም ነበር፡፡ በዚኽ ጉዳይ ላይ ፕሬዝደንት ቡሽ በ1997 ሁለተኛው የምረቃቸው ሥነ-ሥርዓት ላይ ያደረጉት ንግግር ፕሬዝደንት ባራክ ኦባማ ካደረጉት ታሪካዊ ንግግር ሲተያይ "የሚተናነስ" አልነበረም፡፡

"ዛሬ አሜሪካ እንደገና ለዓለም ሕዝቦች ድምፅዋን ታሰማለች፡፡ በጭቆና ሥር ተይዘው እንበለ-ተስፋ የሚኖሩ ሕዝቦች ሁሉ ይኽንን ማወቅ አለባቸው፤ ዩናይትድ ስቴትስ መጨቆናችሁን ዝም ብላ አታይም፡፡ ለጨቋኞችም አድራጎት ምክንያትና ሰበብ አትፈልግላቸውም፡፡ ለነፃነት ስትቆሙ እኛም ከጎናችሁ እንቆማለን፡፡ ለአፈና፣ ለእስር፣ ለስደት የተዳረጉ ዴሞክራቶች ሁሉ ይኽንን መገንዘብ ይኖርባችኋል፡፡ አሜሪካ የእናንተን ማንነት ታውቃለች፡፡ የነገ ነፃ አገራችሁ መሪዎች አድርጋ ትወስዳችኋለች…." ካሉ በኋላ ደግሞ ፊታቸውን ወደ አፋኝ ገዥዎች አዙረው፤ "ሕገ-ወጥ ገዥዎች ደግሞ ዛሬም ቢሆን አብረሃም ሊንከን 'ለሌሎች ነፃነትን የሚነፍጉ ለራሳቸውን ነፃነት አይገባቸውም' ባሉት መርኅ እንደምናምን ማወቅ ይኖርባችኋል፡፡" በማለት "አስጠንቅቀው" ነበር፡፡

የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች እነዚኽን ቃላት ሲሰሙ ልዕለ-ኃያሏ አሜሪካ ከጎናችን ልትቆም ነው የሚል ተስፋ ነበራቸው፡፡ በአፋኞቹ ሠፈር ግን እስከዚኽም ጭንቀት የፈጠረ አይመስለንም፡፡ ስሌታቸው ግልፅ ነበር፡፡ የአሜሪካን መንግሥት በሽብር ላይ አካሂዳለሁ ለሚለው "አጠቃላይ ጦርነት" ከጎኑ ስለቆምንና ስለሚፈልገን ዴሞክራሲን ለማስፈን በሚል ሰበብ በዚኽ በጦርነቶች ለሚናወጥ አካባቢ ያለውን አንድ የተረጋጋና "ወዳጅ" መንግሥት ተፃርሮ ዴሞክራሲም ሰላምም ለማምጣት በማይችሉና ምንም ዓይነት ተዓማኒነት ከሌላቸው ኃይሎች ጎን አይሰለፍም የሚል ፅኑ እምነት ነበራቸው፤ አሁንም አላቸው፡፡ እርግጥ በዚኽም ላይ ቢሆን የቡሽ አስተዳደር በሰላም፣ በአገር መረጋጋትና በዴሞክራሲ መኻከል ስላለው ግንኙነት ቢያንስ በልፈፋ ደረጃ እነሱን አሸማቅቆ የኛን አቋም በሚያስተናግድ መልክ የተቀረፀ ፖሊሲ አለኝ ይል ነበር፡፡ ኮንዶሊዛ ራይስ መንግሥታቸው በመረጋጋት ስም ከእንግዲህ አፋኞችን አቅፎ ደግፎ የሚይዝበትና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል የሚያደናቅፍበት ምንም ምክንያት እንደማይኖር በማብሰር "የሁሉንም ሕዝቦች የዴሞክራሲ ጉጉት" እንደሚደግፉ ከገለፁባቸው ንግግሮች በሰኔ 1997 ዓ/ም በካይሮ ተገኝተው ያስተላለፉትን መልእክት እንደ ምሳሌ ብንወስድ፤

"ላለፉት ስድሣ ዓመታት አገሬ በመኻከለኛው ምሥራቅ የተከተለችው ፖለቲካ ዴሞክራሲን በመረጋጋት ስም የሚሰዋ ነበር፡፡ ሁለቱም አልተሳኩልንም፡፡ አሁን ሌላ ፖሊሲ እየተከተልን ነው…. ዴሞክራሲ ወደ ትርምስ፣ ግጭትና ሽብር ይወስዳል የሚሉ ወገኖች አሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ተጨባጩ ሃቅ የዚኽ ተፃፃሪ ነው፡፡ ጥላቻን፣ መከፋፈልን፣ አመፅን ለማቸነፍ የሚችሉ እሴቶች ቢኖሩ ነፃነትና ዴሞክራሲ ብቻ ናቸው…" ይላል፡፡ (AFP. June 20/2005).

እንደ አጋጣሚ ሆኖ የቀድሞዋ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እነዚኽን ቃላት የሰነዘሩት ሰኔ 97 በአገራችን "በፀረ-ሽብሩ ትግል" ሰበብ አሜሪካ አቅፋ ደግፋ የያዘችው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብለው በተንቀሳቀሱ ወጣቶች ላይ የጥይት ዝናብ የሚያወርድበት፣ ከአርባ ሽህ በላይ ቁጥር ያላቸው ዜጎችን በማጎሪያ ጣቢያዎች የወረወረበትና የዴሞክራሲም፣ የሰላምም፣ የመረጋጋትም ኃይል እንዳይደለ ለመላ ዓለም በይፋ ያሳየበት ወቅት ነበር፡፡ ሆኖም "ከእንግዴህ በመረጋጋት ስም ዴሞክራሲን አንሰዋም" የሚለው አዲሱ የመንግሥታቸው ፖሊሲ በየትም በተግባር ላይ እንዳልዋለ ሁሉ በኛም አገር ሲሠራ አልታየም፡፡

ከዚኽ ተጨባጭ ልምድ በመነሳት የወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ዛሬም ቢሆን በአካባቢው "ለአጠቃላይ ፀረ-ሽብር ትግል" በአካባቢው ከኛ የተሻለ "አስተማማኝ" ኃይል አይገኝም በሚል ስሌት ባራክ ኦባማ ከሳቸው በፊት የነበሩ አስተዳደሮች ይከተሉት የነበረውን ፖሊሲ ሳይቀይሩ ይቀጥሉበታል የሚል ተስፋ አላቸው፡፡ እኛ ደግሞ ከዚኽ መራር ልምድ ተነስተን የዛሬውን የባራክ ኦባማ ንግግር ከነዚኽ ከቀደሙት የአሜሪካ ይፋና በጎ የሆኑ ፖሊሲዎች ስናነፃፅር ስለ ተግባራዊነታቸው እጣ ፈንታ ስናሰላስል መጀመሪያ በኅሊናችን የሚመጣ አንድ ጥያቄ አለ፡፡

ይኸውም "ሰውየው ይኸንን ራእያቸውን በተግባር ይተረጉሙታል ወይስ እንዳለፉት ሁሉ በወቅታዊ ሁኔታ ገዥነት (ሪአልፖለቲክ) ተማርከው ለአሜሪካ ሰላምና ዘላቂ ጥቅም ሲባል 'ከታሪክ አንፃር ተሳስታችኋል' ካሏቸው "አፋኝና ሙሰኛ" ብለው ካወገዟቸው እንደ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ያሉ ኋላ-ቀር ኃይሎች ጋር የማሽበልበል ፖሊሲ ይከተላሉ? የሚለው ጥያቄ ነው:: በኛ ግምት መነሳት ያለበት ወሳኝ ጥያቄ ግን ይኸ አይመስለንም:: ከዚኸ ይልቅ አንስተን መመለስ ያለብን ጥያቄ ትላንት እነ ጆርጅ ቡሽ /ኮንዶሊዛ ራይስ አባባል ሁሉ "በአንድ ራስ ሁለት ምላስ" እንዳይሆን በኛ በኩል ምን አደረግን? ዛሬስ ጥሬዝደንት ባራክ ኦባማ በቃላቸው እንዲፀኑና የአሜሪካን መንግሥት እዛው በዛው ለዴሞክራሲም፣ ለሰላምም፣ ስመረጋጋትም የምናደርገውን ትግል እንዲደግፍ ቢያንስ ቢያንስ ደግሞ ለአፋኙ አገዛዝ እገዛ በማድረግ የሕዝባችንን የሰቆቃ ዘመን ለማራዘም እንዳይተባበር ምን ማድረግ አለብን? የሚለው ይመስለናል:: ይኸ ደግሞ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ይኸ ፖሊሲ ተግባር ላይ እንዳይውል ይረዳናል ብለው ተስፋ ወደ ጣሉበት ወደ አገር-ወዳዱና ዴሞክራቱ የተቃዋሚው ጎራ መዝረክረክና ብቃት ማነስ ጥያቄ ያመጣናል::

ሙሰኞቹና አፋኞቹ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ከዚች ድሃ አገራችንና ለመጠነ-ሠፊ ችግር ከተዳረገ ሕዝባችን ጉሮሮ እየነጠቁ በሚረጩት በደርዘን ሚሊዮን በሚቆጠር ዶላር እገዛ በተቀጣሪ ጉዳይ አስፈጻሚዎች (ሎቢይስቶች) በኩል ለምዕራብ መሪዎች የሚያስተላልፉትን መልዕክት ጠንቅቀን እናውቃለን:: ዴሞክራሲ ቢባል የደርግን ፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ "ኮሙኒስት" መንግሥት አስወግደን፣ በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ መድብለ-ፓርቲ ሥርዓት ያነገሠ ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥት እንዲፀድቅ አድርገናል:: በዚኸ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓትም በመጠቀም በተደጋጋሚ ነፃ ምርጫ እያካሄድንና እያቸነፍን እዚኸ ድረስ ደርሰናል ባዮች ናቸው:: በጠራራ ፀሐይ በመቶ የሚቆጠሩ ዜጎች እየረሸኑ፣ ያለውን የአፈና ፖሊሲ መሸፈን ሲያቅታቸው ደግሞ ይኸንን እርምጃ ለመውሰድ "የተገደዱት" ይኸንኑ "ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት" በአመፅ ለማፍረስ የሚደረገውን ሙከራ ለመቋቋም እንደተወሰደ "ሕጋዊ" እርምጃ አድርገው ያቀርቡታል:: አንዳንድ መንግሥታት ወይም ዓለም-አቀፍ ስብስቦች የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የሚያካሂዱትን ዓይን ያወጣ የሰብዓዊ መብት-ጥሰት ለማውገዝ ሲያቅታቸውም ለዚኸ የተሰናዳ መልስ አላቸው:: "እርግጥ በዚች በመላ ታሪኳ ዴሞክራሲን አይታም ሰምታም በማታውቅ አገር የዴሞክራሲ ግንባታው ሂደት አልፎ አልፎ አንዳንድ ችግሮች ያጋጥሙታል:: ሆኖም ዴሞክራሲ ቀስ በቀስ በሂደት የሚገነባ እሴት በመሆኑ ጊዜ የሚወስድ ነውና ልትታገሱና ጊዜ ልትሰጡ ይገባል..." የሚል ክርክር ደግመው ደጋግመው ይሰነዝራሉ:: በነካ እጃቸው ደግሞ ተቃዋሚ ኃይሎችን እስከነአካቴው ይኸንን ሂደት ለማደናቀፍ ሌላው ቀርቶ ሕገ-መንግሥታዊውን ሥርዓት በአመፅ ለመገልበጥ የሚጥሩ ኃይሎች አድርገው ለመወንጀል ይቃጣቸዋል:: በሰላም ጥያቄም ምንም እንኳን የአሜሪካም የኛም ጠላት የሆኑ ሽብርተኞች ደግመው ደጋግመው ቢፈታተኑንም እነሱን በቁርጠኝነት እየተዋጋን በአካባቢው አንፃራዊም ቢሆን ሰላም የሰፈነባት አገር መሥርተናል:: ተቃዋሚ ነን የሚሉ ኃይሎች ከሕዝብ የተነጠሉ፣ እርስ በርሳቸው የሚቦጫጨቁና ለሥልጣን ቢበቁ አገሪቱን ብሎም አካባቢውን ለባሰ አስከፊ ትርምስ ሊዳርጉ የሚችሉ የጥፋት ኃይሎች ናቸው በሚል ከፍተኛ ዘመቻ ያካሂዳሉ::

በእርግጥ ከምርጫ 97 ወዲህ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች "ዴሞክራትነት" በዓለም-አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የሆነ የተአማኒነት ችግር አጋጥሞታል:: ሆኖም ራሳችንን እናታልል ካላልን በስተቀር አሁንም ይኸ የለየለት አፋኝ ሥርዓት ከጊዚያዊ ችግሮች ባሻገር ".. በሂደት ቀስ-በቀስ በተረጋጋ ሁኔታ የሚገነባ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት" አራማጅ ኃይል ሆኖ የሚታይበት፣ ይኸ ሕዝባችንን በሽብር አፍኖ የያዘው የፀረ-ሕዝብ ጥርቃሞ፣ የፀረ-ሽብሩ አጠቃላይ ጦርነት አስተማማኝ አጋር ሆኖ የሚወሰድበት ሁኔታ ውስጥ ነን:: እንዲኸ ዓይነቱ አስተሳሰብ ዛሬም ቢቀጥል በኛ ድክመት እንጂ በተቀጣሪ ጉዳይ አስፈጻሚዎች (ሎቢይስቶች) ብርታት ወይም በሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች አዋቂነትና ጥንካሬ ምክንያት አይደለም:: ከዚኸ በመነሳት ነው "ባራክ ኦባማ በቃላቸው ረግተው ከጎናችን ይሰለፋሉ ወይስ አይሰለፉም?" የሚለውን ጥያቄ ከማንሳት ይልቅ፣ ልዕለ-ኃያሏ አሜሪካም ሆነች ሌሎች ኃያላን "ዴሞክራሲ፣ ሰላም፣ መረጋጋት" በሚለው አቋማቸው ፀንተው አፋኞችን፣ አሸባሪዎችን፣ ኋላ-ቀር ኃይሎችን በፅናት እንዲቃወሙ እኛ ምን ማድረግ አለብን የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል የምንለው:: ከዚኸ ጥያቄ ስንነሳ ካለፉት አካሄዶቻችን ትምህርት ቀስመን እንራመድ ካልን የሚጠበቅብንን ተግባር ከሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል:: የመጀመሪያው የምናስተላልፈው መልዕክታችን ጥራት ጉዳይ አለ:: ሁለተኛው ደግሞ ይኸንን ጥራት ያለው መልዕክት ተግባራዊ ለማድረግ እንዴት እንንቀሳቀስ የሚለው ጥያቄ መመለስ ይኖርበታል::

ጥራት ያለው መልዕክት ስንል ምን ማለት ነው? በአሁኑ ወቅት በዓለም-አቀፍ ደረጃ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ በአውሮጳም ሆነ በአሜሪካ የፓርላማ አባላት፣ የጋዜጠኞች፣ የሴቶች፣ የተለያዩ የሙያ ስብስቦች መሪዎች በአገራችን ከተራ አፋኝ አገዛዝነት አልፎ ወደ ፍጹም አፋኝና ጨቋኝ (ቶታሊታሪያን) ሥርዓት እየተቀየረ ያለውን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ነጋ-ጠባ ለማውገዝ የተገደዱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ ሆኖም የተቀጣሪ ጉዳይ አስፈጻሚዎችም ሆነ አንዳንድ መንግሥታትና እንደ አውሮጳ ኮሚሽን ያሉ ስብስቦች ችግሩ እንዳለ መካድ ባይችሉም፣ በአገራችን ከዋናው ባለጉዳይ ከሕዝብ ጋር ውይይት አሻፈረኝ ካለው አፋኙ አገዛዝ ጋር "የረጋ ውይይት" በማካሄድ የዴሞክራሲን ችግር በሂደት ቀስ-በቀስ መፍታት ይቻላል የሚል አቋም ሲይዙና አንዳንድ ጊዜ እየተጠየፉትም ቢሆን አፍንጫቸውን ይዘው ከዚኽ መንግሥት ጋር የደራ ግንኙነት ሲቀጥሉ እናያለን፡፡

በያዝነው ወር እንኳ በአንድ በኩል የአውሮጳ ፓርላማ የኢሕአዴግን ፀረ-ዴሞክራሲነት ሲያወግዝ፣ በዚሁ ፓርላማ ውስጥ የተለያዩ ኮሚሽኖች መሪዎች ለአውሮፓ ኮሚሽን ፕሬዝደንት የኢሕአዴግን መሪዎች ፀረ-ዴሞክራሲነት አውግዘው በዚኽ መንግሥት ላይ በተለይ ሰብዓዊ መብትን የማክበር ግዴታን የሚደነግገው የኮተኑ ስምምነት በተግባር እንዲውል ሲጠይቁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኮሚሽኑ ለዚኽ መንግሥት 322 ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ሲለግስ አይተናል፡፡ በዚሁ ሣምንት ደግሞ የካውንስሉ ፕሬዝደንት ጽ/ቤት ጃኑዋሪ 30 ባወጣው መግለጫ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ያወጣውንና ድፍን ዓለም ያወገዘውን ሲቪል ማኅበራትን የሚያኮላሽ አዋጅ በተመለከተ አንዳንድ ዓይን ያወጡ ግድፈቶችን ከጥያቄ ውስጥ ቢያስገባም ዞሮ ዞሮ ይኽ ሕግ የወጣው "የሲቪል ማኅበራት ኃላፊነት የሚሰማው፣ ፍሬአማና ግልፅነት ያለው አሠራር እንዲከተሉ" ለማድረግ እንደሆነ ከገለፀ በኋላ፤ " የአውሮፓ ኅብረት ሕጉ ገንቢ በሆነ መንፈስ ከሥራ ላይ እንዲውል --- በአንድ በኩል በሕጋዊ አሠራርና በለላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ጠንካራ የሆነ ሲቪል ማኅበረሰብ መገንባት አስፈላጊነት መኻከል ሚዛናዊ ግንኙነት ያለው አሠራር እንዲኖር..." ተስፋ ያለው መሆኑን አስቀምጧል፡፡ መግለጫው አልፎ ተርፎ በሌላ ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የፃፉት ይመስል የኢሕአዴግ ፓርላማ በቅርቡ "የአፍሪቃ የዴሞክራሲ፣ የምርጫና የመልካም አስተዳደር ቻርተር" በመፈረሙ የተሰማውን ደስታ ከገለፀ በኋላ፣ ይኽንን ቻርተር ለመፈረም ኢትዮጵያ ሁለተኛዋ አገር በመሆኗ ይቺ አገር "ስለ ዴሞክራሲ ግንባታ ለሌሎች የአፍሪቃ አገሮች በጣም ጥሩ ምሳሌ ሆናለች" በማለት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ዴሞክራሲ ከኛ ተርፎ አፍሪቃን ለማጥለቅለቅ የሚቃጣበት ደረጃ የደረሰ መሆኑን ያበስርልናል፡፡

ከዚኽ ተጨባጭ ሁኔታ ከተነሳን ጥራት ያለው መልዕክት ስንል የመጀመሪያ መጀመሪያ ዲፕሎማሲያዊ ሥራችን ዛሬ በአገራችን "ግንባታ" የሚሉ ነገር ካለ በመገንባት ያለው ዴሞክራሲ ሳይሆን የፍጹም ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ሥርዓት እንደሆነ ማሳየት ይኖርብናል ማለት ነው፡፡ በአገራችን ከዛሬ ይልቅ የዛሬ አምስት ዓመት የተሻለ የዴሞክራሲ ፍንጭ ነበር፣ ዛሬ ያ ወድሟል ሲባል ይኽንን መካድ ሲያቅት ተጨባጩን ክስተት እንደ ጊዚያዊና አላፊ ችግር አድርገው ለማቅረብ ለሚቃጣቸው ወገኖች መልሳችን አጭርና ግልፅ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይኸውም ከአራት ዓመታት በፊት ኢዴፓን የነአቶ መለስ ዜናዊን ሕገ-መንግሥት አስመልክቶ ለዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ባሰራጨው 'ግልፅ ደብዳቤ' እንደተመለከተው "ዛሬ በአገራችን የዳኝነት ነፃነት ባይኖር፣ የሕግ የበላይነት ደብዛው ቢጠፋ፣ የሕዝባችን ሰብዓዊ መብቶች ያለ አንዳች ተጠያቂነት ቢረገጡ፣ አገራችን ባለፈበት ዘመን (defunct era) ሕገ-መንግሥት ሥር በመውደቋ እንደሆነ መታወቅ አለበት" የሚለው መልእክት ነው፡፡

ስለሆነም ስለ ዴሞክራሲ ሂደት (ዴሞክራታይዜሽን) እና ስለ አዝጋሚ ግንባታ የሚደረገውን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ልፈፋ በማያዳግም ሁኔታ ለማጋለጥ በዴሞክራሲው ሂደት ላይ የተጋረጠው የአገራችን ችግር መሠረቱ እነዚኽ ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች የሶቪየቱ ሠፈር ከፈረሰ በኋላ በዓለም ከቀሩት እንደ ቻይና፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ቬየትናም ያሉ እፍኝ የማይሞሉ አገሮች ብቻ ተተክሎ ለቀረ ስታሊናዊ ሰነድ በናሙናነት ሊቀርብ የሚችል ሕገ-መንግሥት ስለተከሉብን እንደሆነ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርብናል፡፡ ከዚኽ አልፎም ኋላ-ቀሮቹ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች በየአምስት ዓመቱ እናዘጋጃለን የሚሉት "ነፃ ምርጫ" መድብለ-ፓርቲ ምርጫን በአንድ ፓርቲ ሕገ-መንግሥት ሥር ለማካሄድ እንደ መግደርደር ያኽል በቅራኔ የተሞላ አካሄድ እንደሆነና በቅርቡ ክብርት አና ጎሜዝ በትክክል እንዳስቀመጡት በዚኽ ሥርዓት ሥር ምንጊዜም ነፃ ምርጫ ሊካሄድ እንደማይችል አስረግጦ መግለፅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚኽ ደግሞ ያለው እንቅፋት ፖለቲካዊ ብቻ ሣይሆን ሕገ-መንግሥታዊም እንደሆነ አበክሮ ማስረዳት የእኛ የዴሞክራቶች ኃላፊነት ነው፡፡ ይኽ ዓይነቱ አካሄድ

በተማፅኖ (ፔቲሽን) በሰላማዊ ሰልፎች፣ በርሃብ አድማዎችና በሌሎች የተቃውሞ ተግባራት የምናደርጋቸውን ዘመቻዎች እንድንተው ያደርጋል ወይም በነዚኽ የመታገያ መንገዶች አንጠቀምም ማለት አይደለም። ይኽንን እያካሄድን ከዚኽ በምንም በማይለይ ሁኔታ በአገራችን ያረጀና ያፈጀ ዘመን ሕገ-መንግሥት የተከሉብን የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች ፕሬዝደንት ባራክ ኦባማ ከታሪክ አንፃር በተሳሳተ ጎራ የተሰለፉ ላሏቸው አገዛዞች እንደ ሁነኛ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ አፋኝና ሙሰኛ ኃይሎች መሆናቸውን የማስጨበጡ ጉዳይ የትግላችን የማይናቅ ገፅታ እንደሆነ ተገንዝበን በሁሉም ረገድ መንቀሳቀስ ይኖርብናል ማለት ነው።

በዲፕሎማሲ ትግላችን የምናስተጋባው መልዕክት ምን ያኽል ጥራት ቢኖረው ፍሬአማ እንዲሆን ከፈለግን ደግሞ አካሄዳችንን መቀየር ይኖርብናል። ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በዚኽ መስክ የምናደርገውን ትግል መና ለማስቀረት የኢሕአደግ ቅጥረኞችም ሆኑ ደጋፊዎች የሚጠቀሙበት ዘዴ የአገር-ወዳዶችንና የዴሞክራቶችን ሠፈር ምንም ዓይነት አንድነት በሌላቸው፣ በሆነ ባልሆነው እርስ-በርሳቸው በሚቦጫጨቁ ኃይሎች የተትረፈረፈ፣ በአገሪቱም ሆነ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት ምንም ዓይነት ተዓማኒነት የሌለው የጥቂት አካራሪዎችና አኩራፊዎች ጎራ አድርጎ ማቅረብ ነው። የእስካሁኑ አካሄዳችን ይኽን ዓይነቱን ክርክር የሚያግዝ እንጂ የሚያፈርስ እንዳይደለ ለሁላችንም ግልፅ ይመስለናል። በመሆኑም ከአለፈው ተምረን ያንኑ አንድ ነገር ለማለት ተበታትነን ከመቅረብ ተወያይተን አንድ የጋራ የድፕሎማሲ ስትራቴጂ መንደፍ፣ ይኽንን ተግባራዊ ለማድረግ አንድ የጋራ የዲፕሎማሲ ዘመቻውን በአጥቂነት የሚያካሂድ ግብረ-ኃይል ሰይሞ በአውሮጳም ሆነ በአሜሪካ እንዲሁም በቀረው ዓለም ሠፊ የሆነ የኢትዮጵያውያን ድጋፍ ያለው እንቅስቃሴ ለመጀመር ቆርጠን መነሳትና መወሰን ይኖርብናል። ይኽንን አድርገን በባዕዳን ኃያላን ፊት በኢትዮጵያ ስም ሊናገር የሚችል አስተማማኝ የሆነ ኃይል ካልፈጠርን ከስመ-ጥፉው የለንደን ጉባዔ ጀምሮ ደግመን ደጋግመን እንዳየነው የአገራችን ዕጣ ፈንታ ባዕዳንና ሳንመርጣቸውና ሳንፈቅዳቸው በሕዝባችን ትከሻ ላይ በተቀመጡ ፀረ-ኢትዮጵያ ጥቂቶች መኻል በሚደረግ ዝግ ውይይት የሚወሰንበት አደገኛ ሁኔታ እንዲቀጥል እያገዝን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ለዚኽም በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል በተግባር የሚገለጽ አጣዳፊ ምላሽ እንዲሰጥ ማሳሰቢያችንና ጥሪያችንን በድጋሜ እናቀርባለን።

አስተማማኝ ድል በጋራ ትግል!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

የካቲት ፳ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ/ም


**ዋና መሥሪያ ቤት** (Main Office)
**ፖ.ሣ.ቁ.**/P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A
**ስልክ ቁ.**/Tel. 202 361 7162

**አውሮጳ** (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
**ስልክ** Tel/Fax 31 70 394 6132